# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ቁጥር 233 ጥቅምት 22 2005 ገጽ 1

**ወያኔ "ግብር" ወይም "ታክስ" ብሎ የሚጠራቸው ነገሮች እውነተኛ ስማቸው "ንጥቂያ" ወይም "ዝርፊያ" ነው። ንብረታችንን ከኪስ አውላቂ የመጠበቅ መብት እንዳለን ሁሉ ከወያኔ ንጥቂያና ዝርፊያ ራሳችንና ንብረታችንን መጠበቅ ተቀባይነት ያለው ሥናይ ተግባር ነው። ለወያኔ ግብር አለመክፈል ራስን ከዘራፊዎች የመከላከልን ያህል የሚያስመሰግን አኩሪ ተግባር ነው።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የወያኔ ፖሊስ መብታችን ይከበር የሚል ጥያቄ ያነሱ የደብረብርሀን ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በቆመጥ ሲደበደብ መዋሉ ተሰማ

የደብረ ብርሀን የኑኒቨርሲቲ አስተዳደር በቅርቡ በስራ ላይ ያዋለዉን አዲስ የዉጤት አሰጣጥ ደንብ ተቃዉመዉ ሠላማዊ ሠልፍ የወጡትን ዩኒቨርሰቲዉ ተማሪዎች በክልሉ የሚገኘዉ የወያኔ ፖለስ አስለቃሽ ጭስ በመጠቀም በቆመጥና በሰደፍ ሲደበድብ መዋሉን በክልሉ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምፅ ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ። የተማሪዎቹን እንቅስቃሴ በቅርብ ሆነዉ የተከታተሉት ምንጮቻችን ከደብረ ብርሀን በላኩልን ዜና መሠረት ተማሪዎቹ የተቃዉሞ ጥያቄዎቻቸዉን ያቀረቡት ለዩኒቨርሲቲዉ አስተዳደር ሲሆን አስተዳደሩ የተማሪዎቹን ህጋዊ ጥያቄ ከመመለስ ይልቅ ዛቻና ማስፈራሪያ በመጀመሩ በሰላማዊ መንገድ የተጀመረዉን የተማሪዎች ተቃዉሞ ዉዝግብና ኃይል ወደ ተቀለቀለዉ ተቃዉሞ እንዲያመራ አድርጓል።

በእለቱ ፖሊስ ተማሪዎቹን ማደሪያ ክፍላቸዉ ድረስ እያሳደደ ባደረገዉ ጭካኔ የተሞላበት ድብደባ አያሌ ተማሪዎች መጎዳታቸዉንና ወደ አካባቢዉ ሆስፒታል ለህክምና መወሰዳቸወን ለማወቅ ተችሏል። የነብስ ወከፍ መሳሪያ፤ ቆመጥና አስለቃሽ ጭስ የያዙ የፌዴራል ፖሊስ አባላት የዩኒቨርሲቲዉን ቅጥር ግቢ ጥሰዉ የገቡት በለሌት በመሆኑ ከፈተኛ ቁጥር ያለዉ ተማሪ ከዩኒቨርሲቲዉ ግቢ እየሸሸ በየቤተክርስቲያኑና በየመኖሪያ ቤቱ ለመጠለል ተገድዷል።

የፖሊስ ተግባር የህዝብን ሠላምና ደህንነት መጠበቅ ሆኖ ሳለ የወያኔ ፖሊስ ግን ስራዬ ብሎ የተያያዘዉ መብቱና ነፃነቱ እንዲከበርለት የሚጠይቅን ህዝብ እየተከታተለ መደብደብ፤ ማሰርና መግደል ነዉ፤ ለዚህም ይህ ዛሬ በእኛ ላይ ያደረሰዉ ድብደባና በቅርቡ አማራ ክልል ወሎ ዉስጥ በግፍ የተገደሉት ሙስሊም ወንድሞቻችን ጉዳይ አይነተኛ ምሳሌ ነዉ ሲል አንድ ስሙ እንዳይጠቀስ የጠየቀ የዩኒቨርሲቲዉ ሠራተኛ ተናግሯል።

## የወያኔን ግፍና መከራ እየሸሹ ከአገር የሚሰደዱ ሰዎች ሞት ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱ ታወቀ

ከዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ግፍና መከራ ሸሽተዉ ከአገራቸዉ የተሰደዱ ሰባ ሁለት ኢትዮጵያዉያን ባሳሶ እየተባለ ከሚጠራዉ የሶማሊያ ወደብ በጀልባ ተሳፍረዉ ወደ የመን ለመግባት ሲሞክሩ ጀልባዋ በድንገት በመስጠሟ የሁሉም ህይወት ማለፉን የየመን የዉጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት አስታወቀ። የሚኒስቴሩ መ/ቤት በባህር ላይ ሲንሳፈፍ የነበረዉን ሟች ኢትዮጵያዉያን አስከሬን በፎቶግራፍ አስደግፎ ባሰራጨዉ በዚሁ ዘገባዉ እንዳመለከተዉ በሁለት መለስተኛ ጀልባዎች የተጫኑ ሰባ ሁለት ኢትዮጵያዉያን ወደ የመን በማቅናት ላይ እንዳሉ በተነሳዉ ከፍተኛ ማዕበል ጀልባዋ በመስጠሟ ሰባ ሁለቱም ኢትዮጵያዉያን መሞታቸዉን አስታዉቋል።

ባለፉት ሀያ አመታት ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ ህዝብ አገሩን እየጣለ ከሚሰደድባቸዉ የአለም አገሮች ዉስጥ በቀዳሚነት ደረጃ የምትጠቀስ ሲሆን በተለይ ከ2005ቱ ምርጫ በኋላ የወያኔ አገዛዝ አፈናና ግፍ በእጥፍ በመጨመሩ በበዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትጵያዉያን በተለይ ወጣቶች አገራቸዉን ጥለዉ እንደሚሰደዱ የተባበሩት መንግስታትና የተለያዩ መንግስታት ጥናታዊ ዘገባዎች ይጠቁማሉ።በዚህ በያዝነዉና ባለፈዉ አመት ብቻ በሰሀራ በረሃ፤በሜደተሪንያን ባህር፤ በማላዊ ሀይቅና በኤደን ባህረ ሰላጤ አካባቢዎች አገራቸዉን ጥለዉ ሲሰደዱ የሞቱ ኢትዮጵያዉያን ቁጥር በሺዎች እንደሚቆጠር የየአካባቢዉ ባለስልጣኖችና የዜና ማሰራጫ አወታሮች በወቅቱ መዘገባቸዉ ይታወቃል።

የየመን የአገር ዉስጥ ሚኒስቴር መ/ቤት በቅርቡ በሰጠዉ ማስጠንቀቂያ እያደገ የመጣዉን ኢትዮጵያዉያን ስደተኞችን ቁጥር ለመገደብ ጠበቅ ያለ እርምጃ መዉሰድ እንደሚጀምር አስታዉቋል። የመን በመኖሪያ ቤት እጦት፤በምግብ ችግርና በአስተዳደር ጉድለትና በሐይማኖት ልዩነት የተነሳ ብዙ ኢትዮጵያዉያን ስደተኞች ከፈተኛ እንግልት፤ እስርና ሞት ከሚደርስባቸዉ አገሮች አንዷ መሆኗ ይታወቃል።

## ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ለግብፅ አንድ ሚሊዮን ስኩየር ሜትር መሬት ለመስጠት መወሰኑ ታወቀ

የወያኔ አገዛዝ ለግብፅ መንግስት አንድ ሚሊዮን ስኩዌር ሜትር መሬት ለመስጠት ስምምነት ላይ መድረሱን አንድ "አህራም አን ላይን" የተባለ ግብጽ ዉስጥ ከፍተኛ ተነባቢነት ያለዉ ድረገጽ ከሰሞኑ በፎቶ ግራፍ አስደግፎ ባወጣዉ ዘገባ አስታወቀ። ይህ ለግብፅ መንግስት የሚሰጠዉ ስፋት ያለዉ መሬት በዬትኛዉ የአገሪቱ አካባቢ እንደሆነ ባይታወቅም ግብፅ መሬቱን የፈለገችዉ ትልቅ የእንዱስትሪ መንደር ለመገንባት መሆኑን የግብፁ ጠ/ሚኒስትር ሀሺም ካንዲ በቅርቡ አልጄሪያ መዲና አልጀርስ ዉስጥ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ አባይ ወንዝ ላይ የህዳሴዉን ግድብ ለመገንባት ከወሰነች በኋላ ቀድሞዉንም ቢሆን አጥጋቢ ያልነበረዉ የግብፅና የኢትዮጵያ ግንኙነት ይበልጥ መሻከሩ የሚታወስ ሲሆን ይህንኑ በማስታከክ አፍቃሬ ወያኔ የሆኑ ድረገጾችና ጋዜጦች የህዳሴዉን ግድብ አስመልክቶ ችግር ልትፈጥርብን ትችላለች እይሉ ግብፅን ሲከስሱ መቆየታቸዉ ይታወሳል።

ይህንን በሁለቱ መንግስታት መካከል የተደረገዉን ስምምነት አንዳንድ ወገኖች የሁለቱን አገሮች የኢንቨስትመንት ትብብር ያሳድገዋል ሲሉ ሌሎች ደግሞ ስምምነቱ ግብፅ በአባይ ወንዝ ላይ ያላትን ጠንካራ አቋም ለማለስለስ የተወሰደ እርምጃ ነዉ ይላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ለግብፅ የሚሰጠዉ መሬት የቆዳ ስፋቱ ነዉ እንጂ መሬቱ የሚሰጠዉ በሽያጭ ይሁን ወይም በስጦታ ምንም የታወቀ ነገር የለም።

የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ለማፈራረስ ቆርጦ የተነሳዉ የወያኔ አገዛዝ እጅግ ሰፋፊና ለም የሆኑ የኢትዮጵያ መሬቶችን በሽያጭና በስጦታ ለተለያዩ አገሮችና ነጋዴዎች ሲቸበችብ እንደቆየ በስፋት መዘገቡ ይታወቃል።

## ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ትግሉን በአዲስ ስልት ሊቀጥሉ እንደሆነ ተሰማ

አፋኙንና ዘረኛዉን የወያኔ አገዛዝ ጭንቀት ውስጥ ጥሎት የቆየው የሙስሊም ኢትዮጵያዉያን ትግል በአዲስ መልክ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሆነ ከአዲስ አበባ የደረሱን ዘገባዎች አመለከቱ። ይህ አዲስ የትግል ስልት ዘረኛው አገዛዝ በሀይማኖት ውስጥ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት ለማስቆም በቅርቡም አገዛዙ በየወረዳዎች ባካሄደው ምርጫ ካድሬዎቹን በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ የሾመበትን ፀረ ህዝብ አሰራር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስወገድ ያለመ እንደሆነ ታውቋል።

አዲስ የተቀየሰው የትግል ስልት ለትግሉ ስኬትና ደህንነት ሲባል በዝርዝር ያልተገለጸ ይሁን እንጂ አዲሱ ስልት ቀደም ብሎ በአዲስ አበባ፣ በታላቁ አንዋርና በቤኒ መስጊዶች ይደረግ የነበረውን ተቃውሞ በተጠናከረ መልኩ በየክልሉ ከተማዎች በሚገኙ መስጊዶች ሁሉ በፈረቃ በማካተት የሚቀጥል መሆኑ ታውቋል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በክልል ከተሞችም በተወሰኑ መስጊዶች ብቻ ይደረግ የነበረዉ የሙብት ማስከበር ትግል በክልሉ በሚገኙ ሁሉም መስጊዶች በየሳምንቱ በፈረቃ እንዲካሄድ፣ የኮሚቴው ተወካዮችም ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ጋር ትግሉን በተመለከተ በየወቅቱ መረጃ ለመለዋወጥ እንደወሰኑ ለማወቅ ተችሏል።

አምባገነኑና አፋኙ የወያኔ አገዛዝ ሙስሊም ኢትዮጵያዉያን እያካሄዱ ያሉትን ትግል ለማፈን እልህ አስጨራሽ ሙካራ ሲያደርግ የቆየና በማድረግ ላይ ያለ ቢሆንም፣ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተጠናከረና እልህ በተሞላበት መንፈስ የወያኔን አፈና በመጋፈጥና በመፋለም ላይ እንደሆኑ በስፋት ሲዘገብ መቆየቱ ይታወቃል።

በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያዉያን የእስልምና እምነት ተከታዮች ይህ ለሙብትና ለነፃነት የሚደረገዉ ትግል ለክርስቲያን ወንድሞቻቸዉና እህቶቻቸዉ በምንም መልኩ ስጋት የሚፈጥር አለመሆኑን በመጥቀስ ይልቁንም ክርስቲያኑና ሙስሊሙ የወያኔን መሰሪ የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ ለማክሸፍ በጋራ እንታገል የሚል ትግል ጥሪ አስተላልፈዋል።

ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሙ ማህበረሰብ እያካሄደ ያለዉን የሙብትና የነፃነት ትግል እንዲቀላቀሉ ተደጋጋሚ ጥሪ ማድረጉ ይታወሳል።

## የወያኔ ግብር - የዘረፋና የመጨቆኛ መሣሪያ

የወያኔ ባለሥልጣኖች፣ "ላም አለኝ በሰማይ" ከሆነው አሰልቺ "ልማት-ተኮር" ዲስኩሮቻቸው በኋላ የምራቸውን ከልባቸው ሲናገሩ የሚደመጡት "አምጡ! ክፈሉ! አዋጡ!" የሚሉትን ቃላት ነው። "የአገር ውስጥ ገቢ" እያሉ የሚያቀላምጡት የዘረፋና የመጨቆኛ ተቋማቸው "ክፈል፤ አለበሊያ እስር ቤት!!!" ማለትን ብቻ ነው አሳምሮ የሚያውቀው። ወያኔ፣ ሥልጣን በጉልበት ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ በግብርና በመዋጮ እንደተሰቃየ ነው።

የወያኔ ግብር ከኪስ አውላቂ ሌቦች ዝርፊያ የባሰ መሆኑ የደረሰበት ሁሉ የሚያውቀው ነው። ዘራፊዎች እጃቸው ውስጥ የገባውን ነገር ይዘው ይሮጣሉ። አንዴ የተዘረፈ ሰው ዳግም እንዳይዘረፍ መዘጋጃ ጊዜ አለው። ወያኔ ግን ተዘራፊው አጠገብ ቁጭ ብሎ ደግሞ ደጋግሞ ይዘርፋል። ወያኔ ከደደቢት በረሃ ወደ ምኒሊክ ቤተመንግሥት ያደረገው ጉዞ ነጥቆ ከመሮጥ ወደ ቁጭ ብሎ መዝረፍ የተደረገ ሽግግር ነው። ዛሬ ወያኔ የመንግሥትን ሥልጣን በጉልበት ይዞ እየፈፀመ ያለው ድሮ በረሃ በነበረበት ጊዜ ሲያደርግ የነበረውን ነው። የተለወጠ ነገር ቢኖር መጠሪያዎች ብቻ ናቸው። ዛሬ ዘራፊዎቹ "ተጋዳላይ" በመባል ፋንታ ደግሞ "ግብር ሰብሳቢ"፣ "ፓሊስ"፣ "የፍርድ ቤት ዳኛ" ተብለው ይጠራሉ።

በሕዝብ ፈቃድ ይመረጡም አይመረጡም መንግሥታት የሚሰበስቧቸው ግብሮች ቢያንስ የሚከተሉትን ዋና ዋና መርሆች ያሟሉ ናቸው።

1ኛ. እኩልነት (በተለያዩ የሥራ መስኮች ቢሰማሩም እንኳን ሁለት ተመሳሳይ ገቢ ያላቸው ሰዎች ተመሳሳይ መጠን ያለው ግብር መክፈል አለባቸው የሚለው መርህ)፤

2ኛ. እርግጠኝነት (የግብር መጠን በአስከፋዩ በዘፈቀደ የሚወሰን ሳይሆን ከፋዩም አስልቶ ሊደርስበት የሚችል መሆን እንዳለበት የሚደነገው መርህ)፤

3ኛ. አመቺነት (የግብር መክፈያ ጊዜና አከፋፈሉ ለግብር ሰብሳቢው ሳይሆን ለከፋዩ አመቺ መሆን ይኖርበታል የሚለው)፤

4ኛ. ወጪ ቆጣቢነት (የግብር አሰባሰቡ ዘዴ ወጪ ቆጣቢ መሆን ይኖርበታል፤ በተለይም የግብር ከፋዮችን ጊዜና ጉልበት ማባከን የለበትም የሚለው)፤ እና

5ኛ. ቀላልነት (የግብር ሥርዓቱ ቀላልና የሂሳብ ሙያ የሌለውም ሰው በቀላሉ ሊረዳው የሚችል መሆን ይኖርበታል የሚለው)። ወያኔ በግብር ስም የሚያደርገው ዘረፋ ግን ከላይ ከተዘረዘሩት መርሆች ውስጥ <u>**አንዱንም**</u> አያሟላም።

የእኩልነት መርህን ብንመረምር ከሌላው ኢትዮጵያዊ እኩል ግብር ሊከፍሉ ቀርቶ ድጎማ የሚደረግላቸው ቅምጥሎች አሉ። ድሃው በግብር ወገቡ ሲጎብጥ፤ የወያኔ ካድሬ ግብር-አልባ ንግዱን ያጧጡፋል። ኤፈርትና ኩባንያዎቹ ለዚህ አብይ ምሳሌዎች ናቸው። የእርግጠኝነት መርህም በወያኔ ዘረፋ ቦታ የለውም። ማጅራት መቺ "ያለህን ዘርግፍ" እንደሚል ሁሉ የወያኔ ግብር ሰብሳቢዎች በጭንቅላታቸው የመጣላቸውን ትልቅ ቁጥር በሚጠሉት ነጋዴ ላይ በግብር እዳነት መጫን የተለመደ ነው። አመቺነትን በተመለከተም ስለ ግብር ሰብሳቢው እንጂ ስለ ከፋዩ ምቾት የሚጨነቅ የለም። ወጪ ቆጣቢነትና ቀላልነትን በተመለከተም ለማመን የሚያስቸግሩ ሃቆችን መዘርዘር ይቻላል። በአስር ሺህ ካፒታል የሚነግድ ሱቅ የአስር ሺህ ብር የሂሳብ ማሽን እንዲገዛ ይገደዳል። የሂሳን ማሽኑን የሚያከፋፍለው ደግሞ የግብር "እፎይታ" የተሰጠው የወያኔ ኩባንያ ነው። በብዙ ወጪና ልፋት የተሰላውን ግብር ለመክፈል ያለውን ውጣ ውረድ፣ ልምምጥና ልመና የደረሰበት ያውቀዋል።

በወያኔ የዘረፋ ግብር ምክንያት የኢትዮጵያ ነጋዴ ሠርቶ የእለት ጉርሱን እንኳን መቻል እያቃተው ነው። ከራሳቸውን አልፈው ለሌሎች ወገኖች ሥራ ፈጥረው የነበሩ በርካታ ወገኖቻችን በዘረፋ ግብር ምክንያት ከስረው ድርጅቶቻቸውን ዘግተው ለስደት ተዳርገዋል። በታሪካችን ነጋዴ የተሰደደበት ጊዜ አሁን ነው። በርካታ የቢዝነስ ሥራ አስኪያጆች በግብር ሰበብ ወህኒ ወርደው ራሳቸው ለእንግልት፤ ቤተሰቦቻቸው ደግሞ ለረሃብ ተዳርገዋል። በወያኔ መዳፍ ሥር ባለችዋ ኢትዮጵያ ከፓለቲካ ቀጥሎ ለእስር የሚዳርግ ሥራ ንግድ ሆኗል። ሥራ ፈጠራ (ኢንተርፕሪነርሺፕ) የሚያሸልም ሳይሆን የሚያሳስር ነገር ሆኗል። ወያኔ፣ ተቃዋሚዎቼ ናቸው ብሎ የሚጠረጥራቸውን የግሉ ቢስነስ ማኅበረሰብ አባላትን ከሚጨቁንባቸው መሣሪያዎች ግንባር ቀደሙ ግብር ነው። ይህንን በየፍርድ ቤቱ የተከፈቱ የግብር ክስ መዝገቦችን በመቃኘት ማረጋገጥ ይቻላል።

"የወያኔ ግብር የዘረፋና የመጨቆኛ መሣሪያ ነው" የምንለው በስሜት ተገፋፍተን ሳይሆን እውነት በመሆኑ እና ይህንንም በበቂ ማስረጃዎች ማረጋገጥ ስለምንችል ነው።

ወያኔ "ግብር" ወይም "ታክስ" ብሎ የሚጠራቸው ነገሮች እውነተኛ ስማቸው "ንጥቂያ" ወይም "ዝርፊያ" ነው። ንብረታችንን ከኪስ አውላቂ የመጠበቅ መብት እንዳለን ሁሉ ከወያኔ ንጥቂያና ዝርፊያ ራሳችንና ንብረታችንን መጠበቅ ተቀባይነት ያለው ሠናይ ተግባር ነው። ለወያኔ ግብር አለመክፈል ራስን ከዘራፊዎች የመከላከልን ያህል የሚያስመሰግን አኩሪ ተግባር ነው።

ስለሆነም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በተናጠልም ሆነ በቡድን ባመቸው መንገድ ሁሉ ተጠቅሞ ወያኔ በግብርና በመዋጮ ስም የሚያደርገውን ዝርፊያ እንዲያመክን ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ጥሪ ያደርጋል። ከወያኔ ዘረፋ ሙሉ በሙሉ መገላገል የምንችለው ራሱ ወያኔን ከሥልጣን አስወግደን ኃላፊነት የሚሰማው በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት ሲኖረን ብቻ ነው። ለዚህ ግብ መሳካት በመደረግ ላይ ባለው ትግል ውስጥ የንግዱ ማኅበረሰብ ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርግ ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወገናዊ ጥሪ ያቀርባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

.....................................................................................................................................

## ከኢትዮጵያ የተዘረፈ 450 ቢሊዮን ብር እንደተከማቸ አንድ የማሳቹሰትስ የኒቨርሲቲ አጋለጠ

አሜሪካ የሚገኘው የማሳቹሰትስ ዩኒቨርስቲ በያዝነው ወር ባወጣው ጥናታዊ ሪፖርት ባለፉት 20 አመታት ውስጥ ከኢትዮጵያ እየተዘረፈ ወደ ውጭ አገራት ባንኮች የተሻገረው ገንዘብ 25 ቢሊዮን ዶላር ወይም 450 ቢሊዮን ብር መድረሱን ይፋ አድርጓል። ይህ አሀዝ ሲሰላ አገሪቱ ካላት አጠቃላይ ገቢ ውስጥ 84 በመቶ የሚሆነውን የሚሸፍን ነው።

ይህ በቅርብ ቀን የወጣ ሪፖርት እንዳረጋገጠው አብዛኛው ገንዘብ የሚዘረፈው ወደ ውጭ አገራት ከሚላኩና ከውጭ አገራት ከሚገቡ እቃዎች እንዲሁም በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው ከሚልኩት ገንዘብ ነው።
በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም ድጋፍ ሰጭነት ተመሳሳይ ጥናት ያካሄደው ፋይናንሻል ኢንተግሪቲ ከዚህ ቀደም አውጥቶት በነበረ መረጃ ባለፉት 7 አመታት ከኢትዮጵያ ከ 11 ቢሊዮን ዶላር ወይም ከ200 ቢሊዮን ብር በላይ መዘረፉን ይፋ አድርጎ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ይህ ሪፖርት በቀረበ አመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ የማሳቹሴትስ ዩኒቨርስቲ አዲሱን አስደንጋጭ ሪፖርት ይፋ አድርጓል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ስልጣን ላይ በቆየባቸዉ ባለፉት ሃያ አንድ አመታት በአንድ በኩል ከፍተኛ የዉጭ እርዳታ ሲቀበል የቆየ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱ የዉጭ ዕዳ መጠን በፍጥነት እያደገ መምጣቱ ብዙዎችን ያስደነገጠ ሀቅ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ ከአገሪቱ የዉጭ ዕዳ ከሁለት እጥፍ በላይ የሚበልጥ ገንዘብ በወያኔ ሹሞችና በቤተሰቦቻቸዉ እየተዘረፈ ከአገር መዉጣቱ በተደጋጋሚ መዘገቡ ታዉቋል።

## ምርኩዛችን ሸንበቆ አይደለም !!!

እግዚአብሄር የፈጠረን በነፃነት እንድንኖር ነው።ነፃነት የጠዋት ፀሃይ ነች። የጠዋት ፀሃይ ስንሞቃት ሰውነትን ደስ እንደምታሰኝ ሁሉ ነፃነትም እንዲሁ ነች። ይህችን እንደ ጠዋት ፀሃይ ደስ የምታሰኝን ነፃነት ሰጥቶ የፈጠረን እግዚአብሄርን ማመስገን ይገባል። ይህች የፈጣሪ ስጦታ የሆነች ነፃነት ባለችበት እውነት አለች። ይህች ነፃነት ባለችበት ተጠያቂነት አለች። ይህች ነፃነት ባለችበት ፍቅር አለች። ይህች ነፃነት ባለችበት መተማመን አለች።ይህች ነፃነት የህልውናችን መሠረት ነች። የህልውናችን መሠረት የሆነችን ነፃነት ተከልክሎ መኖር ሙሉ ሰው ከመሆን ያጎድላል።

የነፃነትን ዋጋ የተረዳና ነፃ የሆነ ማህበረሰብን የሚመራ ሰው ምርኩዙ የማይሰበር የታመነ ነው።የህዝቡን ነፃነት ገፍፎ አገርን እመራለሁ የሚል ግን ምርኩዙ ሸንበቆ፤ የተሰበረ ዕለትም ተመልሶ የሚወጋው ነው። ህወሃት እንዲያ ነው። የዜጎችን ነፃነት ገፎ በጉልበቴ እገዛቸኋለሁ እያለ ነው። ምርኩዙ የታጠቀው መሣሪያ እንጂ ህዝቡ አይደለም። ይህ ታጠቅን ብለው የሚመኩበት መሣሪያ የሸንበቆ ምርኩዝ ነው። በዚህ መሣሪያ አስገድጄ ህዝብን እገዛለሁ የሚል ቡድን ሲሰበር ተመልሶ የሚዋጋን የሸንበቆ ምርኩዝ ተመርኩዞ የቆመ አንካሳ ሰውን ይመስላል።የህወሃት አቋም እንዲያ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ልጅ ከፈጣሪ የተሰጠውን ታላቅ ስጦታ አስነጥቆ መኖርን እሺ ካለ ያተርፍበት ዘንድ የተሰጠውን መክሊት  መሬት ምሶ የቀበራትን ያንን  ሰነፍ ሰው ሆነ ማለት ነው። ነፃነታችን ሠርተን ፍሬ አፍርተን እንኖርባት ዘንድ የተሰጠችን ዋጋ ያላት መክሊት ነች። ነፃነት ፍሬዋ በገንዝብ አይተመንም እንጂ ብዙ ሚሊዮን ዋጋ ባወጣች ነበር።ነፃነታችንን ሰጥቶ የፈጠረን እግዚአብሄር ስንት ያወጣል እንደማይባል ሁሉ ነፃነታችንም በገንዘብ የምትገመት አይደለችም። ህወሃት ሊፈጠራት በሚሞክራት ኢትዮጵያ ግን ነፃነታቸውን ለገንዘብ ሲሉ አሳልፈው የሚሰጡ ለራሳቸው ክብር የሌላቸው ግለሰቦች እንደ አሸን ፈልተዋል። ነፃነት ለድርደር የሚቀርብ ነገር አልነበረም። ነፃነታችንን ሰጥተን የምንቀበለው ሌላ ምንም ነገርም አልነበረም። ህወሃት ግን የዜጎችን ነፃነት በሚበላና በሚጠጣ ከንቱ ነገር ገዝቶ አገሪቷን ለመምራት ይሞክራል። ይሄ ዘረኛ ድርጅት ምኞቱ ዜጎች ነፃነታቸውን ተነጥቀው ዝም ብለው  ከሰው ተራ ጎድለው እንዲኖሩ ነው። ይሄ ደግሞ ለራሳቸው ክብር በሚሰጡ ዜጎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው አይደለም።ለራሱ ክብር የሚሰጥ ሰው ነፃነቱን ተነጥቆ ዝም አይልም እንዲያውም "ነፃነቴን ወይም ሞቴን" ብሎ ይነሳል።

ዛሬ በአገራችን ደምና አጥንታቸውን ቆጥረው የተደራጁ ራሳችውን "የትግሬ ነፃ አውጪ" ብለው የሚጠሩ ቡድኖች የእግዜር ስጦታ የሆነችውን ነፃነታችንን ነጥቀው ከሰው ተራ አጉድለው ሊገዙን ተማምለዋል። ለዚህም መሃላቻው ለሚበላ እና ለሚጠጣ ከንቱ ነገር ብለው መኪልታቸውን የሸጡላቸውን አልባሌ ሰዎች ከጎናቸው አሰልፈዋል። እነዚህ ቡድኖች የነፃነትን ዋጋ ሳያዋቋት ነፃ አወጣናችሁ ይሉናል። እነርሱ ሁሉን አድራጊ ሁሉን ፈጣሪ፤ እነርሱ ሰጪና ከልካይ መሆን መቻላቸውን ነፃነት ብለው ይጠሩታል። ይሄም ምንኛ ከዚህ ዘመን ጋር አብረው መሄድ የማይችሉ የጭለማ ንጉሶች እንደሆኑ አመላካች ነው። እነዚህ የጨለማው ነገስታት በምንም መሠፍረት አገራችንን ለመምራት የሚመጥኑ አይደሉም።አገራችንና ዜጎቿ ከህወሃት በላይ በጣም ከፍ ያሉ ናቸው።ለዚህም ነው የአዲስ አበባ ወጣቶች ትንሽ የሚተነፍሱበት አጋጣሚ ባገኙ ግዜ "ሳንፈልጋቸው ሃያ ዓመታቸው" እያሉ ያዜሙት።

ህወቶች ነፃነትን አያውቁም። ነፃነት ያለውን ህዝብም ለመምራት ብቃት የላቸውም። ምርኩዛቸው ህዝብ ሳይሆ የያዙት የመሣሪያ ብዛት፤ እምነታቸው እውነት ሳይሆን ውሸት ነው። በመሣሪያ ብዛት እና በውሸት ላይ ቆሞ እስከ መጨረሻው መዝለቅ እንደማይቻል በዙሪያቸው ከሚከሰተው ሁኔታ አንኳ መማር የማይችሉ ልበ ደንዛዞች ናቸው። ተመርኩዘው የቆሙት የሸንበቆ ምርኩዝ ነገ ሲሰበር ተመልሶ እንደሚወጋቸው ለመረዳት ብርቱ የሆነ የአስተሳሰብ ችግር አለባቸው። የነገውንም አርቀው ለማየት አቅም ያላቸው አይደሉም። እነዚህን ቡድኖች ለምኖና ተማጽኖ ነፃነትን ማግኘት ስለማይቻል የተነጠቅነውን ነፃነታችንን የምናስመልሰው ከምር በመታገል ብቻ ነው። ነፃነታችንን ዘረኞቹ ህወሃቶች የሚሰጡን እኛም የምንለምናቸው ሊሆን አይገባውም። ነፃነታችን የተፈጥሮ ስጦታችን ነው።

እኛ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ የተነሳነው ህወሃት የነጠቀንን ነፃነታችንን ለማስመለስ ነው። ከነፃነታችን የሚበልጥ ምንም ነገር የለም።ነፃነታችን ክብራችን፤ነፃነታችን እስትንፋሳችን ነች። ነፃነታችንን አስነጥቀን ዝም አንልም። "ነፃነት ወይም ሞት" ብለን ተነስተናል፡፡ ለነፃነት የሚከፈለውን መስዋእትነት ሳናቅማማ ለመክፈል ዝግጁዎች ነን። የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ነፃነታችንን ለማስመለስ በምናደርገው ትግል ውስጥ ያዋጣናል ብለን ባመንበት በማንኛውም መንገድ ሁሉ እንሄዳለን። ሁለገብ ትግል ስንልም አሉ የሚባሉ ግን ደግሞ በህወሃት ላይ ጫና ፈጥሮ አገሪቷን ሊታደግ የሚችለውን ማንኛውንም የትግል ስልት እንጠቀማለን ማለታችን ነው። በዚህ ትግል ውስጥ ሊረዱን የሚፈልጉ ወዳጆች ካሉ እርዳታው ለትግላችን እስከ ጠቀመን ድረስ አመስግነን እንቀበላለን። የሚረዱንን ወዳጆች የምንመርጠው እኛ እንጂ ህወሃቶችና ከእነርሱ ጎን የተሰለፉ ቡድኖች አለመሆናቸውን በዚህ አጋጣሚ ልናሳውቃቸው እንፈልጋለን። ዘረኛው ህወሃት ቀይ መስመር ያሰምርልን ዘንድ እድሉን አንሰጠውም።

ህወሃት አገራችን ያፈራቻቸው ነውረኛ ግለሰቦች ስብስብ ነው። እነዚህ ነውረኞች በዘረኝነት መጋራጃ ተጋርደው የነገውን ማየት ተስኗቸዋል።ከተጋረዱበት ዘረኝነት ወጥተው ዓይናቸውን ይገልጣሉ ማለትም አይቻልም። ያን ግዜና ሁኔታ ማለፋቸው ብቻ ሳይሆን ተፈጥሯቸው ከዘረኝነት ውጪ ሌላ ህይወት ሌላ ፖለቲካ እንዳለ ማየት አያስችላቸውም። ያለን አማራጭ የተጋረዱበትን የዘረኝነት መጋረጃ አስገድዶ በመግለጥ ዓይናቸውን ከፍተው አርቀው እውነትን ማየት እንዲችሉ ማድረግ ነው።

አዎን ነፃነታችንን የገፈፈንን ዘረኛ ቡድን አስገድደን ዓይኑን እንዲከፍት ለማድረግ በዚህች ምድር የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ቆርጠን ተነስተናል።ለድልም የሚያበቃን እውነት ከእኛ ጋር አለ። ምርኩዛችን ተሰብሮ የሚወጋን ሸንበቆ አይደለም። ምርኩዛችን የፍትህ፤ የነፃነት እና የእኩልነት ጥያቄ ነው። እነዚህ ጥያቄዎች የመኖራችን ህልውናና ሰው የሚያደርጉን የማዕዘን አለቶች ናቸው። ነፃነታችን ያለምንም ገደብ እስከሚከበር ድረስ የጀመርነውን ትግል ግንባራችንን ሳናጥፍ እንቀጥላለን እንጂ ለአፍታም ቢሆን አናፈገፍግም።

የተከበራችሁ ወገኖቻችን ለነፃነት፤ለፍትህ እና ለእኩልነት በምናደርገው ትግል ውስጥ እንድትቀላቀሉን ደግመን ደጋግመን ጥሪያችንን እናቀርባለን።ከተባበርንና ለጥያቄዎቻችን በአንድነት መልስ መፈለግ የምንችል ከሆነ የትግሉን እድሜ ማሳጠር እንችላለን።መለያየትና እርስ በራስ መነቃቀፍ የሚጠቅመው ዘረኛ ህወቶችን እንጂ ነፃነቱን ተነፍጎ ከሰው ተራ ጎድሎ የሚኖረውን ህዝባችንን አይደለም። ለነጻነት ለሚደረገው ትግል አንዳችም እርባና በሌለው ንትርክ ውስጥ ግዜን ማጥፋት ሥራ የፈታ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል እንደሚባለው መሆን ነው።እዚህ ላይ አበቃን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ሀይለማርያም ደሳለኝ አሁንም ካቢኔ መመስረት አልቻለም፣ ምክንያቱ ህወሀት ነዉ ተባለ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የህወሀትን አባላት የአመለካከት መዛባት ለማጥራት በሚል በየክልሉ ግምገማ የጀመረ ሲሆን ይህ የተጀመረ ግምገማ ወደየቀበሌዉ ወርዶ እከሚጠቃለል ድረስ ሀይለማሪያም ደሳለኝ የራሱን ካበኔ መመስረት እንዳልቻለ ኢሳት ቴሌቪዥን ዉስጥ አዋቂ የኢህአዴግ ምንጮችን በመጥቀስ ዘገበ።

ኢሳት ቴሌቪዥን በዚሁ ዘገባው እንደገለጸው በአሁኑ ጊዜ ህወሀት  የአባላቱ አመለካከት እየተጣራና ፣ የአዲሱን ጠቅላይ ሚኒሰትርና እና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሹመት አይቀበሉም የተባሉትን አካላት ለማግለል እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው።

በድርጅቶች መካከል በተነሳው አለመግባባትም  ሀይለማርያም ደሳለኝ እስካሁን ድረስ ካቢኔውን ሊሰይም ካለመቻሉም በላይ በተለይም የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅትን የሚያረካ ስልጣን መጥፋቱ፣ ሀይለማርያም ስልጣኑን ተጠቅሞ ካቢኔውን እንዳይሾም እንዳደረገው ጥቆማ የደረሰው መሆኑን ኢሳት ገልጿል።

የዘረኛው አምባገነን የወያኔ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ከሞተ ወዲህ በወያኔ ኢሃዴግ ድርጂቶች ውስጥ ያለው ሽኩቻና መፈረካከስ በስፋት እየቀጠለ መሆኑ በስፋት ሲዘገብ መቆየቱ ይታወሳል።

---

## የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ላይ የጥፋት ዘመቻውን ቀጥሏል፣ አወሊያ ኮሌጅን ጨምሮም ስምንት ምግባረ ሰናይ ድርጅቶችን መዝጋቱ ታወቀ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የአገሪቱን ህግ አክብረዉ ሲንቀሳቀሱ የነበሩትን የእስልምና ጥናት ምርምር ማዕከልንና የአወልያ ኮሌጅን የምዝገባ ፈቃድ መሰረዙንና ድርጅቶቹ እንዲዘጉ መወሰኑን ከአዲስ አበባ የደረሰን ዘገባ አመለከተ። የአገዛዙ የበጎ አድርጎት ማህበራት ምዝገባ ኤጀንሲ ቃል አቀባይ ሰሞኑን አዲስ አበባ ዉስጥ ለጋዜጠኞች በሰጠዉ መግለጫ መሠረት ኤጀንሲዉ የገንዘብ አያያዝ ጉድለት አሳይተዋል ያላቸዉን ስምንት ምግባረ ሠናይ ድርጅቶችንና ከህላፊነታቸዉ ዉጭ በማይመለከታቸዉ ጉዳይ ላይ ጣልቃ እየገቡ ይሰራሉ የላቸዉን የእስልምና ጥናት ምርምር ማዕከልንና የአወልያ ትምህርት ቤትን የስራ ፈቃድ በመሰረዝ ተቋሞቹ እንዲዘጉ ትዕዛዝ አስተላልፏል።

በሌላም በኩል ከዚሁ ጋር በተያያዘ የወያኔው አሻንጉሊት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ባለፈዉ ሰኞ ጥቅምት 19 ቀን ማእከላዊ ፖሊስ ጣቢያ በእስር ላይ የሚገኙትን የኢትዮጵያ ሙስሊም ችግሮች መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ እና የሀይማኖት መብታችን ይከበርልን ባሉ ሼሆችና ኡላማዎች ላይ የፌደራሉ አቃቢ ህግ የመሰረተውን ክስ መስማቱ ተመልክቷል።

የአዲስ አበባ ዘጋቢዎቻችን እንደዘገቡት ይሄው የወያኔ የይስሙላ ፍርድ ቤት የ31 ሙስሊም ተከሳሾችን ጉዳይ የማየት ድራማውን ሲጀምር አቃቤ ህግ ተብዬዎቹ የክስ ፋይሉ ማህተም ይቀረዋል በማለታቸው ችሎቱ ተቋርጦ እንደነበር የታወቀ ሲሆን የወያኔው አቃቢ ህግ ለሸክም ያስቸገረ 26 ጥራዝ የክስ ፋይል እና አባሪ ሰነዶችን በፌደራል ፖሊስ አሸክሞ ማቅረቡ ታውቋል።

ኢትዮጵያዉያን የእስልምና እምነት ተከታዮች ላለፉት አስራ አንድ ወራት አወሊያ ኮሌጅ የራሱን ቦርድ መርጦ በነፃነት እንዲደራጅና መንግስት ከእስልምና እምነት ተቋሞች ላይ እጁን እንዲያነሳ አጥብቀዉ በመታገል ላይ ያሉ መሆኑ ይታወቃል::

ይህ በእንዲህ እንዳለለ በሀሰት ክስ ንጹሃን ዜጎችን በማንገላታት የሚታወቀው የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያ ዉስጥ ስር የሰደደዉን የመብትና የነፃነት ረገጣ አስመልክቶ ለአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች መረጃ ታቀብላላችሁ የሚል የፈጠራ ክስ በመሰንዘር በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ጉባኤና በኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ላይ ይህ ነዉ የማይባል ጫና ማድረግ በማደረግ ላይ መሆኑም ታዉቋል።

## ወያኔ ዳያስፖራዉ በማይኖርበት አዲስ አበባ አበባ ዉስጥ "የኢትዮጵያ ድያስፖራ" ማህበር መሰረትኩ አለ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ባለፈዉ ሳምንት መገባደጃ ላይ ጥቂት ለሆዳቸዉ ያደሩ ግለሰቦችን ሼራተን ሆቴል ዉስጥ ሰብስቦ የድያስፖራ ማህበር አቋቋምኩ ብሎ ማወጁ ተሰማ። "ላም ባልዋለችበት ኩበት ለቀማ" እንደሚባለዉ ወያኔ ድያስፖራዉ በማይኖርበት ቦታ የድያስፖራ ማህበር ማቋቋሙን የገለጸዉ ከዚህ ቀደም አሜሪካ ዉስጥ መጥቶ ተቀባይነት አጥቶ በተለመሰዉ በብርሐኔ ገብረክርስቶስ ማካይነት እንደነበር ከአዲስ አበባ የደረሰን ዜና ያስረዳል። ባለፉት ሦስት አመታት ከሰስትና ከአራት ግዜ በላይ ዋሺንግተን ዲሲና በተለያዩ የአሜሪካ ከተሞች ዳያስፖራዉን ለማግባባት መጥቶ ተዋርዶ የተመለሰዉ ብርሐኔ ገብረክርስቶስ ዛሬ አዲስ አበባ ዉስጥ የዳያስፖራ ማህበር አቋቋምን ማለቱ ማንን ለማታለል እንደሆነ ባይታወቅም የወያኔ አገዛዝና የኢትዮጵያ ድያስፖራ ፍትህ፤ዲሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶችን በተመለከተ ለረጂም ግዜ የዘለቀ የሻከረ ግንኙነት እንዳለቸዉ ይታወቃል።

የወያኔ አገዛዝ ላለፉት ሀያ አንድ አመታት የኢትዮጵያን ህዝብ የመደራጀትና የመሰብሰብ መብት ረግጦ ህዝብን ሲያስር፤ ሲገድልና ከአገር ሲያሳድድ መከረሙ እየታወቀ በሚገኝበት ሁኔታ በሰሜን አሜሪካ፤ በአዉሮፓ፤ በአዉስትራሊያና በመካከለኛዉ ምስራቅ አገሮች እንዳሰፕዉ መደራጀት የሚችለዉን የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ጭራሽ በማይኖርበት አዲስ አበባ ዉስጥ ማህበር አቋቋመ ብሎ መግለጫ ማዉጣቱ የራሱን ደጋፊዎች ጭምር ያስገረመ አስቂኝ ድራማ ነዉ ሲሉ ብዙ የፖለቲካ ታዛቢዎች ትችታቸዉን ሰንዝረዋል።

የወያኔ አገዛዝ መለስ ዜናዊ ከመሞቱ በፊትም ሆነ ዛሬ የኢትዮጵያን ድያስፖራ በተለያዩ ጥቅማጥቅሞች በመደለል በኢትዮጵያ ህዝብና በዳያስፖራዉ መካከል ያለዉን የትግል አንድነት ለመከለስና ለማደካም ከፍተኛ ሙከራ ሲያደርግ መቆየቱ የሚታወስ ነዉ።

### ወግድልኝ ወዲያ

ሲጭኑህ አጋሰስ፤
ሲጋልቡህ ፈረስ፤
ጠምደው ሲያርሱህ በሬ ...
ስትታለብ ጥገት፤
በቁም ሲያርዱህ ሙክት፤
ሲጣልልህ ውሻ - የጅ ዕባሽ ናፋቂ፤
አዳሪ ለሆዱ - ክብሩን አስነጣቂ፤
ጫንቃህ የደለበ - ለመሸከም ቀንበር፤
እንቢኝን የማታውቅ - ከእሽታ በቀር፤
እንዳህያ ጭነት - ሸክም ያስለመዱህ፤
ሲገፉት ነፃነት - የማይበርደው ገላህ፤
አጎንባሽ ለመጣው - የሞትክ ነህ በቁም፤
ወግድልኝ ወዲያ ጭራሽ አላውቅህም!
እንዳንተ ያለውን አገሬ አትናፍቅም።

የአያት የቅድም አያት - ጀግንነቱ ቀርቶ፤
ሸለላ፤ ፉከራው - ዕምቢልታ ቀረርቶ፤
በጦር ደረት መብሳት - ቢጋሻ መክቶ፤
አሻፈረኝ ማለት - ለበደል ለጥቃት፤
በጀግንነት መሞት - ላገር ለነፃነት፤
መሆኑ ቀረና፤
የጀግና ልጅ ጀግና፤
ሰብዕናህ ተገፎ - ዝቅ ብለህ ወደታች፤
ባይተዋር ያገሩ - የበይ ተመልካች፤
ውሎ ጦም አዳሪ - የሀብቱ ተመጽዋች፤
እራስከን ዝቅ አርገህ - ክብርህን ያዋረድክ፤
የት ቦታ ተዘርተህ አገሬ ላይ በቀልክ?!
ወግድልኝ ወዲያ ጭራሽ አላውቅህም!
ለወለደህ ዕዳ ላገርህ ነህ ሸክም።

ንቀት ብርድል ብስህ፤
ውርደት ሆኖ አንሶላህ፤
ነፃነት ሲገፉህ - ዝም ብለህ የተኛህ፤
ጭቆና ተስማምቶ - የማይቆረቁርህ፤
በደል የተመቸህ - ጥላቻ እማይገባህ፤
ዕንቢኝን የማታውቅ - እሺን ያስለመዱህ፤
ኧረ ለመሆኑ ከወዴት ተገኘህ?!
የቱ አባት አግኝቷት - ከምን ጉድ ጸነሰች፤
የቷ እናት አምጣ - ኩቶ አንተን ወለደች?!
እንዳንተ ያለውን ወልዳ ከምታፍር፤
ምንኛ ደስ ባላት - ጨንግፊህ ብትቀር?!
አላውቅህም ጭራሽ ወግድልኝ ወዲያ!
እንዳንተ ያለውን አትሻም ኢትዮጵያ!!

(አሥራደው ከፈረንሣይ)

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org